በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የስ/መ/ቁጥር---229247
ቀን፦ ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም

ለሞቹ፦ ብርሃኑ አመነዉ

ረታ ቶሱሳ

በዕዉቀት በላይ

ቀንዓ ቂጣታ

ኑሪዲን ከድር

አመልካቾች፦ አቶ ምትኩ አበሻ ጠበቃ ፋሲካ በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፦ የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ያለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ ማስመለስን የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው። በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪ ክሳሽ ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ። የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 97205 ሕዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ሕዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 282138 መጋቢት 16 ቀን 2014 ዓ.ም ብይኑና ዉሳኔዉን በማጽናት የሰጠዉ ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ።

ተጠሪ መስከረም 07 ቀን 2014 ዓ.ም ያቀረበዉ ክስ በአጭሩ፦ ተጠሪ የከባድ መኪና ሹፌርና ባለሙያ ለመቅጠር ባወጣዉ ማስታወቂያ መሠረት አመልካች ተመዝግቦና ተወዳድሮ አልፎ የቅጥር ፎርማሊቲ አሟልቶ ከኅዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በወር ደመወዝ ብር 8,555 እየተከፈለዉ ለመስራት የቅጥር

ዉል ፈጽመዋል። ሆኖም ውጣ ዝ በማለት አመልካች በሥራ ዝርታዉ ላይ በአግባቡ ሊገኝ ባለመቻሉ በተደረገበት ክትትል በተመሳሳይ ሞያ በተመሳሳይ የስራ ሰዓት ደርሳ ሜድርክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተቀጥሮ የሚሠራ መሆኑ ተደርሶበት ከየካቲት 14 ቀን 20121 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ተሰናበተበት ጥቅምት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ለ8 ወራት ያህል ከሕግ ዉጭ ደመወዝ ሁለት ቦታ የተከፈለዉ በመሆኑ በተጠሪ የተከፈለዉን የተጣራ ደመወዝ ብር 47,446.94 ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል እንዲወሰንበት ጠይቋል።

አመልካች ለክሱ በሰጠዉ መልስ ክሱ የአሠሪና ሠራተኛ ሆኖ ሳለ በፍትሐብሔር ችሎት ክስ መቅረቡ ተገቢ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ሰማየት ስልጣን የለዉም። ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ከ2 ዓመት በ3ላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሆኗል፤ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል። እንዲሁም በሕጉ አግባብ የከፈለዉን ክፍያ ተመላሽ ይደረግልኝ በማለት ያቀረበዉ ክስ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ የክስ ምክንያት የለዉም ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል። በፍሬ ጉዳይ መልሱ ደንቡ ተጠሪ ደመወዝ ይከፍለኝ የነበረዉ ሥራዉን በአግባቡ ስላከናወነ መሆኑን፤ ለተሠራ ሥራ የተከፈለዉን ደመወዝ በሌላ መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ነበር በሚል መልሰህ ከፈል ሊባል አይችልም። ስለሆነም ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል።

ተጠሪ በበኩሉ በአመልካች ለተነሱት የመጀመሪያ ደረጃ መቋወሚያ ክስ ሲሰማ በሰጠዉ መልስ ክሱ ያላግባብ የመባልጸግ ክስ በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታገድም። ጉዳዩ ከዉል የመነጨ ስለሆነ ይርጋዉ የሚታሰበዉ በመደበኛ የዉል ይርጋ 10 ዓመት ነዉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል።

ጉዳዩ በዚህ አግባብ የተረበለት የፈደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉን መርምሮ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ከትዮር ዉል የመነጨ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163(1) መሰረት የይርጋዉ ጊዜ አንድ ዓመት ሲሆን የይርጋዉ ጊዜ መቆጠር የሚገባዉ የትዮር ዉሉ ከተቋረጠበት ጥቅምት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን ደርሳ ሜድርክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግ/ማሕበር የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ.ም ደብዳቤ ለተጠሪ ከተጻፈበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከተረበበት መስከረም 07 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ 6 ወር ከ7 ቀናት በመሆኑ የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ አልሞላም በማለት መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል። በመቀጠል በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮና መርምሮ ተጠሪ ሁለት ቦታ ተቀጥሮ ደመወዝ ሲቀበል መቆየቱ ያላግባብ መባልጸግ ብቻ ሳይሆን ከትን ልቦናና ከአንድ ሠራተኛ ከሚጠበቅ ስነ-ምግባርና ታማኝነት በሚቃረን መልኩ በተመሳሳይ ሰዓት ሁለት መስሪያ ቤት ሠርቻለሁ የሚለዉ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ለ8 ወራት ያህል ያለአግባብ የተከፈለዉን ብር 47,446.94 ዉሳኔዉን ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም ለደኝነት የተከፈለ ብር 1,760.50 እና የተለያየየ ወጪ ብር 2,500 ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል። በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ አመልካች ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የፈደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በትዕዛዝ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ አጽንቷል። አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ሰማስለወጥ ነዉ።

ማ ሲታወቂ፡ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለተናትና ምርምር ሥራ ወይም ለተገዛዜ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163 መሰረት ከአንድ ዓመት በኃላ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ሲሆን ተጠሪ የስራ ዉሉን ያቋረጠዉ ከጥቅምት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ነዉ። ተጠሪ ለአመልካች ደመወዝ የከፈለዉ ከሳኒቲት 14 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ ነዉ። የመጨረሻ ክፍያ ከተከፈለበት ክስ እስከተመሠረተበት ጊዜ ድረስ ሁለት ዓመት ያለፈዉ ሲሆን ዉሉ ከተቋረጠ ደግሞ ከ23 ወር በኃላ የቀረበ ነዉ። ክሱ በይርጋ ቀሪ ነዉ መባል ሲገባዉ የሰር ፍ/ቤት የይርጋዉ መቆጠር የሚጀምረዉ ደርሳ ሜድርክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ.ም ደብዳቤ ከጻፈበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ በማለት አንድ ዓመት ሳይሞላዉ የቀረበ ክስ ነዉ ሲል በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠዉ ብይን የአዋጁን አንቀጽ 165 የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌን ያላገናዘበ ነዉ። በተጨማሪ ተጠሪ ደመወዝ የከፈለዉ ለተሠራ ሥራ በመሆኑ ገንዘቡ ሊመለስ የማይገባዉ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡ ይመለስ የሚል ክስ ማቅረብ የሚችለዉ ተጠሪ ሳይሆን ሜድርክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነዉ። ስለሆነም የሰር ፍ/ቤት የሰጠዉ ብይንም ሆነ ዉሳኔ እንዲሻር የሚጠይቅ ነዉ።

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በሰር ፍ/ቤት የተጠየቀዉ ጻኘነት ያለአግባብ ለሁለተኛ ጊዜ የወሰዱት የደመወዝ ክፍያ ይመለስልኝ የሚል ሲሆን የሰር ፍ/ቤት በ6 ወር ይርጋ አይታገድም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስተርባል የተባለ ነዉ።

ተጠሪ ጥር 04 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 2 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- ተጠሪ ለአመልካች ያለአግባብ የፈጸመዉ ክፍያ ብር 47,446.94 ተመላሽ እንዲሆን ያቀረበዉ የክስ አቤቱታ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ይርጋ የሚሸፈን ሳይሆን በመደበኛ የፍትሐብሔር ሕጉ የሚገዛ ነዉ። ምክንያቱም አመልካች እንዲይዘዉ የታሰበዉ መኪና ጋራጅ ዉስጥ ለሰርቪስ የገባ መሆኑን አጋጣሚ በመጠቀም አልፎ አልፎ ራርማ ብቻ በመፈረም ለ8 ወራት ደመወዝ ተከፍሎታል። ስራ የተቀጠረዉ ሥራ ለመስራትና ለመቀጠር ሳይሆን ክፍያዉን ለመዉሰድ ነዉ። ምክንያቱም መኪናዉ ለሥራ ዝግጁ ሆኖ ሲፈለግ ባለመገኘቱ ከመታወቂያም በላይ ምንም ዓይነት ሥራ ሳያሠራ በአካዉንቱ ገቢ የተደረገ በመሆኑ ያለአግባብ የበለጸገበትና የወንጀል ፍሬ ያሰዉ ደርጊት ነዉ። ስለሆነም ተፈጻሚ የሚሆነዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 የተመለከተዉ የ10 ዓመት ይርጋ ነዉ። አመልካች በሥራ ዝርታዉ ላይ ሊገኝ ባለመቻሉና ኪሊራንስ ያላመጣ በመሆኑ ክትትል ሲደረግበት ደርሳ ሜድርክ ሲሚንቶ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ.ም ለተጠሪ በጻፈዉ መልስ ተቀጣሪ ሠራተኛዉ መሆኑን አረጋግጧል። ስለሆነም ያለአግባብ ሁለት ቦታ ደመወዝ ሲቀበል ስለነበረና የሕጉወጥ ድርጊቱ ዉጤት ተጠቃሚ ሊሆን ስለማይገባ በአዋጁ አንቀጽ 163 የተቀመጠዉ የ6 ወር ይርጋ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለዉም። ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ ይርጋ የ10 ዓመት ነዉ ተብሎ የሰር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸና የሚጠይቅ ነዉ። የሰበር አመልካች ጥር 25 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 2 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርቧል።

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል። የሰበር አቤቱታዉ ያስተርባል

ማ ሲታወቅ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለተናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዘቢ አገልግ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- በስር ፍ/ቤት የተጠየቀዉ ጻንኝት ያለአግባብ ለሁለተኛ ጊዜ የተከራላቸዉን የደመወዝ ክፍያ ይመለሱልኝ የሚል ሆኖ የስር ፍ/ቤት ክሱ በ6 ወር ይርጋ አይታገድም በማለት መወሰኑ ተገቢ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ።

በመሠረቱ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163(1) በትጥር ላይ ከተመሠረተ ግንኙነት የመነጨ ማንኛዉም ክስ የጊዜ ገደቡ በአዋጅ ወይም አግባብ ባለዉ ሌላ ሕግ በሌላ አኳኃን ካልተወሰነ በስተቀር የመብቱን ጥያቄ ለማቅረብ ከሚቻልበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል በማለት ሲደነግግ የይርጋ አቆጣጠርን የተመለከተዉ የአዋጁ አንቀጽ 164(1) ደግሞ በአዋጅ በተለየ አኳኃን ካልተገለጸ በስተቀር የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረዉ በመብቱ ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለዉ ቀን ጀምሮ ነዉ በማለት አስቀምጧል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ በመርህ ደረጃ በትጥር ላይ ከተመሰረተ ግንኙነት የመነጨ ክስ የይርጋ ጊዜዉ አንድ ዓመት መሆኑን፣ ከአንድ ዓመት ሊበልጥም ሆነ ሊያንስ የሚችለዉ በአዋጁም ሆነ በሌላ ሕግ በግልጽ ክሱን ለማቅረብ የተሰዩ የይርጋ ጊዜ የተቀመጠ እንደሆነ ሆኖ ይርጋዉ መቆጠር የሚጀምረዉ ደግሞ በመብቱ ለመጠቀም ከሚችልበት ወይም ክስ መመስረት ከሚችልበት ቀን ቀጥሎ ካለዉ ቀን ጀምሮ የሚቆጠር መሆኑን ነዉ። ከዚህ ዉጪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሁኔታ ተከስቶ ክስ መመስረት በሚቻልበት ሁኔታ ማስረጃ ለመሰብሰብ የወሰደዉ ጊዜ ታሳቢ ተደርጎ የይርጋ መቆጠር የሚጀምርበት ቀን የሚራዘምበት አግባብ የለም።

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረበዉ ክስ አመልካች በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት ድርጅቶች ተቀጥሮ ሁለት ደመወዝ የተከፈለዉ በመሆኑ ያለአግባብ የከፈለዉ ደመወዝ እንዲመለስለት ሲሆን ምንም እንኳ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ያለአግባብ የመበልጸግና ይርጋዉ 10 ዓመት መሆኑን የተከራከረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ክሱ በትጥር ላይ ከተመሠረት ግንኙነት የመነጨ መሆኑን በማሳየት የይርጋዉ ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 163(1) መሰረት አንድ ዓመት መሆኑን አረጋግጧል። ይህን በመቃወም በተጠሪ የቀረበ መስተሰኛ የሰበር አቤቱታ ካለመኖሩም በላይ በትጥር ላይ በተመሠረተ ግንኙነት ተከፈለ የተባለዉ ደመወዝ እንዲመለስ የቀረበ ክስ ከትጥር ግንኙነት የመነጨ በመሆኑና በአዋጁም ሆነ በሌላ ሕግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ ባለመኖሩ የይርጋዉ ጊዜ አንድ ዓመት ነዉ ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት አግባብ የለም።

በሌላ በኩል በአዋጁ አንቀጽ 164(1) ድንጋጌ መሠረት የይርጋዉ ጊዜ ከመቼ ጀምሮ ነዉ የሚቆጠረዉ የሚለዉን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ አመልካች ሁለተኛ የትጥር ዉል መፈጸሙንና በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት ድርጅቶች ደመወዝ የተከፈለዉ መሆኑን አረጋግጦ የትጥር ዉሉን ካቋረጠበት ከጥቅምት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን ደርባ ሜድርክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ.ም ለተጠሪ ድርጅት አመልካች ከጥቅምት 24 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጣሪ ሠራተኛዉ መሆኑን ካረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ክስ እስከተመሠረተበት መስከረም 07 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ያለዉ ጊዜ 6 ወር ከ7 ቀናት በመሆኑ የአንድ ዓመት ይርጋ ጊዜ አልሞላም በሚል ነዉ። ሆኖም ተጠሪ አመልካች በተመሳሳይ ጊዜ ሁለት

ማ ሲታወቅ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለተናትና ምርምር ሥራ ወይም ለተጨማሪ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም


Click Ethiopian Laws